
Nile 8th year; publication No.2; Feburary, 2022


# ናይል



Nile 8th year; publication No.2 Feburary, 2022 ናይል 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 2፣ የካቲት 2014 ዓ.ም




## እንኳን ለ126ኛው የአድዋ ድል በዓል አደረሳችሁ!




በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጅ ተቋም ዲዛይነርነት የነጭ የሀገር ልብስ በመልበስ የሀገር ፍቅርን፤ ነጭ በመልበስ ድምቀትና የቀዳማዊ ባለቤትነት ስሜትን ለማሳደግ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነጭ የባህል ልብስ በየሳምንቱ አመራሩ፤ በየወሩ ሰራተኛው የመልበስ ስነ-ስርዓት ቀጥሏል።



ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ሚኒስተር ጋር ያደረገው የስራ ስምምነት

ገፅ 4

በውስጥ ገፆች

ከአውሮፓ ህብረት ጋር የተደረገ ው ውይይት
ገፅ 4

Thinking out of the box: Tips for university leader
Page 7

የተማሪዎች የፈጠራ ውጤት
ገፅ 9

ነገረ ሂስ
ገፅ 11

ከጅኦስፔስ ሳይንስ ተመራማሪው ጋር የተደረገ ቆይታ
ገፅ 15

# ናይል

በኢንፎርሜሽን ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነት እና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን
titibdu@gmail.com

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

አለባቸው አለሙ
ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ
ባንቹ ታረቀኝ
ሽጋው መስፍን

**አርታኢ**

ግርማው አሽብር

**ፅሁፊ**

መልሰው አደመ
አበባ ካሰው

**አምደኞች**

ደስታ ተከስተ
አስራት ደርብ

**ስርጭት**

አለነ ጋሹ
አልማዝ አምበሉ
ኑኑሽት ምትኩ
ትርንጎ ወለላው
ወርቅነሽ አበባው
ቀራለም አድማሱ

**ፎቶግራፈሮች**


ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ
አገሬ ዘለቀ

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ
አራጋው በሪሁን (ቸሬ)

አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ የካቲት 2014 ዓ.ም

www.bdu.edu.et
www.facebook.com/bduethiopia
www.twitter.com.bdu.et
+251583206059



# ርዕሰ-አንቀጽ

## የነፃነት ልክ አድዋ … የመስዕዋትነት ጥግ ሞት

ነፃነትን መሻት በህይወት ከመኖር በላይ ነው፡፡ በ1803 እ.ኤ.አ በሰሜን አሜሪካ ጆርጂያ ግዛት Dunbar Creek on St. Simons Island ወንዝ ላይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ ከአፍሪካ ታድነውና በሠንሠለት ታስረው በጠባቡ የመርከብ ጭነት ውስጥ ለወራት ታጉረው ከድካም፣ከበሽታ ከርሀብና ውሀ ጥም ባጠቃላይ ከአሠቃቂ ሞት ተርፈው አሜሪካ የደረሱት ወደ 75 የሚደርሱ የኢግቦ ጎሳ አባላት ለባሪያ ገበያ ለመቅረብ ወደ ትንሽ ጀልባ ተጫኑ፡፡ እነዚህ ከወራት በፊት ነፃ የነበሩ አፍሪካዊያን በባይተዋር ምድር እንደ ዕቃ የሰው ንብረት ሆነው ከሰው በታች ከመኖር ነፃ መውጣትን በማለም እምቢ በማለት አሽጋጋሪ የነበሩትን ሁለት የታጠቁ ሠዎች በሠንሠለት በተጠፈረ እጃቸው ገጥመው አሳሪዎቻቸውን ጨምረው ወደ ወንዙ ወለል በመስጠም የነፃነት መዝሙር እየዘመሩ በጀግንነት ራሳቸውን ሠውተዋል፡፡ በዚህ የመሰዋትነት ጥግ ወይም ሞት ከዘላለማዊ ባርነት መንፈሳቸውን አርነት አውጥተው ያለ ነፃነት በህይወት መኖርን ትርጉም አልባ አድርገውታል፡፡ ታሪክ ይህንን ክስተት ‘Igbo Landing’ ብሎ ይጠራዋል እኔ ደግሞ አጠጋግቸ የኢግቦዎች ማረፊያ አልኩት፡፡ ለብዙ ነፃነታቸውን የተነፈጉና በባርነት ቀንበር ውስጥ ለወደቁ ጭቁኖች የነፃነት ተስፋ ሆኖ አልፏል፡፡

በ15ኛው ክፍለ ዘመን አፍሪካዊያንን በግዳጅ በመውሰድና ብዙ ገንዘብ ለከፈለ እንደ ዕቃ በመሸጥ በባሪያ ንግድ የጀመረውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን 1884 እ.ኤ.አ በርሊን ኮንፈረንስ የፀደቀው የቅኝ ግዛት ስምምነት በ14 የአዉሮፓ አገራት መሪዎች ፊርማ አፍሪካን የመቀራመት እቅድ ነደፉ፡፡ ከስምምነቱ በኋላ የአፍሪካዊያንን ነፃነት ሙሉ በሙሉ ወሰዱ ፤ የአዉሮፓዊያን ሚና ሙሉ በሙሉ ገዥ ወደ መሆን አደገ ፡፡ አፈናዉና ኢ-ሰብዓዊነቱ ሠዎችን ከአህጉረ አፍሪካ ከመስረቅ ወደ መግዛት እንዲሁም የሃገራቱን ሃብት ያለከልካይ ወደ መመዝበር ተሸጋገረ፡፡ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ስር ወደቁ ህዝቦቻቸውም ያለነፃነት በግፍ ለመኖር ተገደዱ፡፡

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አስከፊ የተባለው የቅኝ ግዛት ስምምነት ነጮችን የበላይ ጥቁሮችን የበታች፤ ነጭነት ታላቅነት ጥቁር መሆን ዝቅተኝነትና ተገዥነት መሆኑን አወጀ፤ በ1896 እ.ኤ.አ አድዋ የተሠኘ የጥቁር ነፃነት ፀሐይ እንስኪወጣ ድረስ ዓለም እንደ ህግ ተስማምቶበት ህይወት ቀጥሎ ነበር፡፡

ከ1895-1896 እ.ኤ.አ የተካሄደውና በንጉስነገስት ሚኒሊክ II እና በንግስት ጣይቱ የተመራው የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያዊያን ለሀገር ክብርና ለትውልድ ነፃነት የተከፈለ የህይወት መስዕዋትነት ነው፡፡ “Giving your life is the ultimate sacrifice” እንዳለው Fernando Mateo. የአድዋ የድል ነፃነት ፀሀይ በምስራቅ ታየ ፤ የባርነት ጭልማ ተገፈፈ ፤ የባሪያና የጌታ የነጭና የጥቁር መለያ ግድግዳ ፈረሰ ፤ የሠው ልጅ እኩልነት ተረጋገጠ፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ሁሉም ሰው እኩል ነው ፤ ነጭ፣ ጥቁር ፤ አፍሪካዊ፣ አውሮፓዊ የሚባል እርከን የለም፡፡

ህይወታቸውን ያለስስት በጀግንነት ሰጥተው ነፃነትን ባጎናፀፉን አባቶቻችንና እናቶቻችን ምክንያት አንገታችንን ቀና አድርገን በነጭ ቆዳ ቀለም ሳንደግጥ በነፃነት እንኖራለን፡፡ በአድዋ የወጣው የኢትዮጵያ ፀሀይ ለአለም ጥቁሮች እና ጭቁኖች ብርሃን ሲሆን በቆዳ ቀለም የበላይነት ለሚያምኑት በሙሉ ደግሞ ንዳድ ሆኖባቸው የወራሪው ጣልያን ህዝቦች አደባባይ ወጥተው ‘ቪቫ ሚኒልክ’ ‘ቪቫ ጣይቱ’ ብለዋል፡፡ አሁንም ንጉስ ለሆነው ሚኒልክ ቪቫ ሲያንሰው ነው፡፡ ሚኒልክ ዛሬም ንጉስ ፤ ጣይቱ ዛሬም ብርሀን ዘ- ኢትዮጵያ፡፡

## ዝክረ አድዋ፤የባሕል ኮንፈረንስ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ

በሙሉጌታ ዘለቀ

በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂውማኒቲ ፋኩልቲ አዘጋጅነት ዝክረ አድዋ ፤የባሕል ኮንፈረንስ “የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ ማንነት እና የባህል ልዕልና” በሚል መሪ ቃል የካቲት 17/2014 ዓ.ም በዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በድምቀት ተካሄደ ::

የውይይት መድረኩን በንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ ፕሬዝዳንት ዶ/ር እሰይ ከበደ የአድዋ ድል ሀገራችን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተያዘች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር እንድትሆን ያደረጋት በመሆኑ ዛሬ እኛ በየሄድንበት ሁሉ አንገታችንን ቀና አድርገን እንድንናገር አድርጎናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ የአድዋ ድል የፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝ ፍላጎት የከሸፈበት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ያካሄዱት ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል አብይ አካል እንደነበር ማሳያ ጭምር ነው ሲሉ ዶ/ር እሰይ ተናግረዋል፡፡

የዘንድሮን 126ኛውን የአድዋ ድል በዓልን ስናከብር ካለፉት ዓመታት የተለየ የሚያደርገው አንደኛ አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ቡድን ሀገርን የማፍረስ ሴራው በዘመቻ ለህብረብሔራዊ አንድነት አማካኝነት የከሸፈበት፣ ሁለተኛ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመጀመሪያው ዙር ሀይል የማመንጨት ስራ የጀመረበት በመሆኑ እና ተቋማችን ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተመሰረተበትን 60ኛ ዓመት በድምቀት ለማክበር ዝግጅት እያደረገ ባለበት ወቅት የሚከበር በዓል በመሆኑ ከምንግዜው በእጅጉ የተለየ በዓል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ከቀረቡት ጥናታዎ ፁሁፎች መካከል ፤ የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ የአድዋው ድል ሚስጢር “ስውር ማግኔት” በሚል ርዕስ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሠርጸ ፍሬስብሃት ለአድዋ ድል; የአዝማሪዎች ሚና፣ የፍልስፍና ምሁሩ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ “ዓድዋ በቅኝ ገዢ መንፈስና በነጻነት መንፈስ መካከል የተካሄደ ትግል“ በሚል ርዕስ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለ ፈለገ ሰላም የስነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አገኘሁ አዳነ ደግሞ “አርበኝነት ድልና ገድል በሥነ-ሥዕል” በሚል ርዕስ የሆኑ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ከመርሀ ግብሩ ተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

አውደ ጥናቱ 126 ኛ የዓድዋ ድል በዓልን የሚዘክረው እና የአሁኑ ትውልድ ከድሉ ብስራት ዐሻራ ምን ሊወርስ ይገባል የሚል ዓላማ ያለው እና በርካታ የዩኒቨርሲቲው መምህራን እና ተማሪዎች እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች በንቃት የተሳተፉበት ነበር ::

በመጨረሻም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ሰፋ መካ በአውደ ጥናቱ የመዝጊያ ስነ-ስርዓት ላይ እንዳሉት የአድዋ ድል የአንድነትና የአሸናፊነት ድል በመሆኑ ሀገራችን አሁን ካለችበት ወቅታዊ ችግር ልትላቀቅ የምትችለው የጥንት ጀግኖች አባቶቻችን የመጣባቸውን ሀገራዊ ችግር በጀግነትና በድል የተወጡበትን መንገድ በመከተል፤ የአሁኑ ትውልድ ያጋጠመውን የእርስ በርስ ፤አለመግባባት በማስወገድ የአድዋ የድል በዓልን በጠንካራ ሀገራዊ መንፈስ ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡



በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ኦዲትሪዩም አዳራሽ ዝክረ አድዋ የባህል ኮንፈረስ ሲካሄድ

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል




## በኢትዮጵያ የአውሮፓ ህብረት ልዑክ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አመራሮች ጋር ተወያየ

በወንዳለ ድረስ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አመራር ከአውሮፓ ህብረት ልዑካን ጋር ተወያየ።

በኢትዮጵያ የአውሮፓ ሕብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ የተመራ የአውሮፓ ሕብረት ልዑካን ቡድን ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ጋር በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ፅህፈት ቤት ውይይት አካሂዷል።

ሁለቱ ቡድኖች በአማራ ክልል ስላለው አጠቃላይ አሁናዊ ሁኔታ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሰላም፣ መልሶ ግናባታና መልሶ ማቋቋም ዙሪያ እያበረከቱት ስላለው ሁለገብ አስተዋፅዖ ተወያይተዋል።

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዘውዱ እምሩ በዩኒቨርሲቲው እና በአውሮፓ ሕብረት አባል አገራት መካከል ያለውን የረጅም ጊዜ ግንኙነት ገልፀው በአማራ ክልል በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ በማቋቋም ረገድ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን አስረድተዋል። ገለፃውን ተከትሎም በሁለቱ ወገኖች መካከል ፍሬያማ የሐሳብ ልውውጥ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ የአውሮፓ ሕብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ ሰላምን ወደነበረበት በመመለስና ግጭቶችን በመቅረፍ ስራዎች ላይ ተቋማቱ በጋራ ለመስራት ባላቸው ቁርጠኝነት ዙሪያም ምክክር አካሂደዋል።



የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ እና የኢፌዴሪ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር በለጠ ሞላ

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ

በሙሉጎጃ ም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ እና የኢፌዴሪ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር በለጠ ሞላ የካቲት 3/2014ዓ/ም በባሕር ዳር ከተማ በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ።

በፊርማ ስነስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ክቡር ሚኒስትሩ ዶ/ር በለጠ ሞላ ሁለቱ ተቋማት ችግር ፊች የሆኑ ተግባራትን ያከናውኑ ዘንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከፊርማ በዘለለ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ አክለውም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ሆነ ሚኒስተር መስራያ ቤቱ ስምምነቱን ልዩ ትኩረት ሰጥተው እንደሚተገብሩት እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል።

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በርካታ ወጣት ተመራማሪዎች ስላሉት ለምርምር ማነቆ የሆኑትንለይቶ በማውጣት በምርምሩ ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ በማስገንዘብ ስምምነቱ ወደ ተግባር ተቀይሮ ሁለቱ መስሪያ ቤቶች በመደጋገፍና በመናበብ ልዩ ልዩ ችግር ፈች ተግባራን እንዲያከናውኑ ታልሞ የስምምነት ሰነዱ ስለተፈረመ ለወደፊት በየሩብ ዓመቱ ስራዎች የደረሱበትን ሁኔታ መገምገም እንደሚገባ ተናግረዋል።

በፊርማ ስነስርዓቱ የሚኒስቴሩ ልኡክ እና የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ ሲሆን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽን ስትራቴጅክ ኮምኒኬሽን ም/ፕሬዜዳንት ዶ/ር ዘውዱ እምሩ ዩኒቨርሲቲው ከአጋር አካላት ጋር በመስራት ለረጅም ጊዜ የካበተ ልምድ እንዳለው በመግለጽ ከአሁን በፊት ከ41 አገራት በላይ በጋራ ስምምነት መስርቶ እየሰራ ያለ አንጋፋ ተቋም እንደሆነ ተናግረዋል።


# ጃን ሞስኮብ ቤተ-መጽሃፍት

ከገፅ 14 የቀጠለ

በጠቅላላ ከ2000 ተጠቃሚዎች በላይ በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ እንዲችል ተደርጎ የተገነባ ነዉ፡፡

በጃን ሞስኮብ ቤተ-መጽሃፍት በርካታ አገልግሎቶች የሚሰጥ ሲሆን ለአብነት ያህል የ24 ሰዓት የንባብ አገልግሎት፣ የዉሰት አገልግሎት፣ የማጣቀሻ አገልግሎት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት፣ የዲጂታል አገልግሎት ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ቤተ-መፃህፍቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ያሉትና በዋናነት በ2 ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነዉ፡፡ እነዚህም የቴክኒካል እና የቴክኒካል ያልሆኑ ክፍሎች ሲኖሩት የየራሳቸዉ አስተባባሪዎች የተመደበላቸው ናቸው፡፡ የቴክኒካል ክፍሉ የካታሎግ እና አኮዚሽን ክፍልን በዋናነት የያዘ ሲሆን የቴክኒካል ያልሆነ ክፍሉ ደግሞ የፍተሻ እና ሰርኩሌሽን ክፍልን የያዘ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዲጂታል ቤተ-መፃህፍት የe-books አገልግሎትን እና የምርምር ፅሁፎችን በቤተ-መፃህፍቱ ሲስተም በኩል ለተጠቃሚዎች ያደርሳል፡፡



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የባሕር ዳርን የቴክኒክ ኢንስቲትዩት መርቀው ሲከፍቱ (ሰኔ ወር 1955ዓ.ም)

የቤት-መፃህፍቱ ተጠቃሚዎች መብቶችን በተመለከተ በአጭሩ ለመግለፅ ያህል ማንኛዉም ቋሚ እና ኮንትራት የአካዳሚክ ቅጥር መምህራን ከተመደቡበት የትምህርት ክፍል ደብዳቤ ሲያቀርቡ በቅደም ተከተላቸዉ እስከ 10 (አስር) እና 5 (አምስት) መፃህፍትን መዋስ ይችላሉ::

ተማሪዎችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲዉበሁሉም ፕሮግራም ትምህርታቸዉን ለሚከታተሉ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለእያንዳናዳቸዉ 5 (አምስት) የማዋሻ ፓኬቶች ይሰጣቸዋል፡፡ የቀን የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ደግሞ የ1ኛ እና 2ኛ ዓመት ተማሪዎች 2 (ሁለት) መፃህፍትን እንዲሁም የ3ኛ፣ 4ኛ እና ተመራቂ ተማሪዎች በሙሉ 4 (አራት) መፃህፍትን መዋስ ይችላሉ፡፡

በአንፃሩ በዩኒቨርሲቲዉ ተመዝግበዉ የተከታታይና የርቀት ትምህርት የሚከታተሉ የድግሪ ተማሪዎች መታወቂያቸዉን እያሳዩ የንባብ አገልግሎት ብቻ እንዲያገኙ ይደረጋል::

የአስተዳደር ሰራተኞችን በተመለከተ ቋሚ የአስተዳደር ሰራተኞች 2 (ሁለት) መፃህፍትን መዋስ ሲችሉ ኮንትራት የአስተዳደር ሰራተኞች ደግሞ ዋስ ሲያቀርቡ 2 (ሁለት) መፃህፍቶችን መዋስ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል የዉጭ ተጠቃሚዎች ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ በግል ወይም በቡድን የጥናትና ምርምር ስራን ለማከናወን የድጋፍ ደብዳቤ ለሚያቀርቡ በነፃ የንባብ አገልግሎት ያገኛሉ::

በተጨማሪም የቤተ-መፃህፍት አባል ለመሆን አገልግሎት ለሚጠይቁ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች በቤተ መፃህፍቱ የተዘጋጀዉን ፎርም ሞልተዉና የዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብር 300 (ሶስት መቶ) ብር በመክፈልለተወካያቸዉ 5 (አምስት) ፓኬቶች እንዲሰጣቸዉ ተደርጎ በዉሰት አገልግሎት ደንቡ መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

የቤተ መፃህፍት አባል ለመሆን አገልግሎት ለሚጠይቁ ግለሰቦች የዋስትና ማረጋገጫ ሲያቀርቡና የዓመት አገልግሎት ክፍያ ብር 50 (ሀምሳ) በክፈል ከንባብ አገልግሎት በተጨማሪ 2 (ሁለት) ፓኬቶች እንዲሰጣቸዉ ተደርጎ በዉሰት አገልግሎት ደንቡ መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ተቋም “ጃን ሞስኮብ” ቤተ-መፃህፍት በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ ታላላቅ ቤተ-መጻፍት ውስጥ አንዱ እንጂ ብቸኛው አይደለም፡ ፡ ሌሎችን በቀጣይ ህትመቶቻችን የምንመለስበት ሲሆን ማንበብ ሙሉ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ሀገርና ሙሉ ተስፋ እንዲኖረን በማድረግ የተሻለ ትዉልድ እንዲፈጠር ያደርጋል እንዳልነው አስቀድመን ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋልና ወደ ጃን ሞንኪብ ብቅ ብለው መጽፍትን ይተዋወቁ::

## የናይል እንግዳ ከገፅ 15 የቀጠለ

ብዛታቸው ሊቀያየር ይችላል::

ይህን የመቀያየር ምክንያት እኛ ብቻ ሳንሆን አሜሪካም፣ አውሮፓም ጭምር ያሉ ሰዎች መቆጣጠር የሚያስችል መሳሪያዎችን ተክለን እየተጠቀምን ነው ያለነው:: ስለሆነም የቅንጣት አካላቱ ባህሪ ለምን እንደሚቀያየር እስካሁን ድረስ ማወቅ አልተቻለም:: ከጊዜ ጊዜ፤ ከቦታ ቦታ በተለያየ መጠን እንዲገኙ ያስቻላቸው ነገር ምን እንደሆነ እስካሁን ድረስ በደንብ አልታወቀም:: የላይኛው የአየር ክልል ላይ የሚገኙ ቅንጣት አካላት መቀያየር በተለይም አፍሪካ አካባቢ ያለው ከሌላው አካባቢ የተለየ ነው::

ለኛ የጥናት ፕሮጀክት መነሻችን ይህ ነው:: በመሳሪያ የተደገፈ ጥናት ተደርጎም የመጨረሻው ድምዳሜ ላይ አልተደረሰም:: ሌሎች ሀገራት ያሉ አጥኚዎችም ትክክለኛ ምክንያቱ ላይ አልደረሱም::

በጥናት ፕሮፖዛል ዝግጅቱ በአማካሪነት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እና ዶ/ር እንዳወቅ ይዘንጋዉ ተሳትፈዋል:: በመቀጠልም ይህን ፕሮፖዛል ፈንድ ለሚያደርገው የአሜሪካ አየር ኃይል አስገብተን ተቀባይነት አግኝቶ ከአንድ ሳምንት በፊት ነው አሸንፋችኋል የሚል ደብዳቤ የደረሰኝ:: በዚህ ጥናት በተባባሪ ተመራማሪነት የሚሳተፉ ሰዎች አሉ፡ እነሱም ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እና ዶ/ር አምበሉ ተባባል ናቸው:: እኔ ደግሞ የፕሮጀክቱ ዋና ተመራማሪ ነኝ::

ናይል፡- የፕሮጀክቱ ሀገራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው? ዶ/ር መልሰው፡ - የዚህ ፕሮጀክት ሀሳብ ተቀርፆ በአለም ላይ ስመ-ጥርለሚባለው የአሜሪካን ኢርፎርስ ተቋም ተልኮ በተቋሙ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የገንዘብ ድጋፍ ማስገኘት ማስቻሉ አንድ ትልቅ ውጤት ነው:: ሀሳብን ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬም በዶላር ማስገኘት ተችሏል፡፡ ፕሮፖዛል በመቅረጽና በማቅረብ ብቻም የውጭ ምንዛሬ ማግኘት እንደሚቻል ተሞክሮ ተገኝቶበታል፡፡ ይህ ጥናትና ምርምር ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና ለአገራችንም ትልቅ እሴት ጨምሯል:: የተገኘው ገንዘብ ቢያንስ ከአምስት በላይ የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ማስተማር ያስችላል:: በአጠቃላይ ሲታይ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ሰው መፍጠርና ገንዘብ ማስገኘት ተችሏል::

የሚጠናው ጥናት ደግሞ ታትሞ ጥቅም ላይ ይውላል:: በዚህ ጊዜ ደግሞ በእውቀት ላይ የተመሰረተ እሴት ይጨምራል ማለት ነው::

እነዚያ ቅንጣት አካላት በጊዜና በቦታ ምክንያት እንዲቀያየሩ የሚያደርጋቸውን ምክንያት በጥናት በማስደገፍ በሂሳብ ቀመር ጭምር አስልቶ ማስቀመጥ ይቻላል::

ያን የሂሳብ ቀመር በመጠቀም የሚያደናቅፉት የቅንጣት አካላት የሚፈጥሩትን ማደናቀፍ መጀመሪያ ቢደናቀፍም እኛ ስንጠቀመው ግን እንዳልተደናቀፈ አስመስለን መስራት ይቻላል ማለት ነው::

በውትድርናው አለም ያለውን ሳይንስ ስናየው በሚሳኤል ቦታ የሚመታው ኤክስ ዋይ ኮርድኔት ከታወቀ ብቻ ነው:: ይህ የጥናት ውጤትም ለዚህ አይነት ተግባር ይውላል ማለት ነው::

ናይል፡-የተገኘው የምርምር ፕሮጀክት ለተመራማሪዎችና ለተማሪዎች ምን ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል?

ዶ/ር መልሰው ንጉሤ፡- ተመራማሪዎች በዚህ ፕሮጀክት እንዲደገፉ ይደረጋል::ተማሪዎችንም በተግባር ልምምድ የተደገፈ ስልጠና ሰጥቶ ውጤታማ የጥናትና ምርምር ስራዎችንእንዲሰሩ ማድረግ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በፕሮጀክቱ የተገኘው ገንዘብ ተጋባዥ ተመራማሪዎችንም ለማምጣት ያግዛል:: ለምሳሌ አሁን ያለውን ራዳር አሁን ካለበት ወደ ተሻለ ደረጃ እና ስራ ማሸጋገር ቴክኖሎጅውንም የመልመድና የማሳደግ ጥቅሞች አሉት::

ናይል፡- ፕሮጀክቱን ወደ ተግባር ለመቀየር ምን ሊሰራ ታስቧል?

ዶ/ር መልሰው ንጉሤ፡- በፕሮጀክቱ የተገኘው ገንዘብ ለሦስት አመታት የሚቆይ ሲሆን ከየካቲት አንድ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል:: በአጠቃላይ የተገኘው ገንዘብ 285,608 ዶላር ነው የሰጡን:: አሁን ባለው የአገራችን ምንዛሬ ሲሰላ ከ14 ሚሊዮን ብር በላይ ነው::

ይህን ሀሳብ ወደ ተግባር ለመቀየር በግብዓትነት የምንጠቀማቸው የሰው ኃይል ይኖራሉ:: ሳተላይቶች የሚሰበስቡት መረጃም ይወሰዳል:: ይህን ሁሉ በአንድ ላይ አጣምረን ነው ይህንን ፕሮጀክት ለመተግበር በምክረ-ሀሳብ ደረጃ የተቀመጠው::

ናይል፡- ወደ ተግባር ሲገባ የምርምር ስራውን ስኬታማ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት እና ከዩኒቨርሲቲው ምን ይጠበቃል?

ዶ/ር መልሰው ንጉሤ፡- ተመራማሪዎች ንድፈ ሀሳቡን በደንብ ተጠቅመው ጊዜና ትኩረት ሰጥተው የምርምርና ፈጠራ ስራዎችን በደንብ መስራት ይጠበቅባቸዋል:: የዩኒቨርሲቲው አመራር ደግሞ እንደከዚህ ቀደሙ ሊደግፈን ይገባል::

የተገኘዉ ገንዘብ ገቢ የሚሆነው ወደ ዩኒቨርሲቲው አካውንት ነው:: ስለዚህ እኛ ገንዘብ ለጥናትና ምርምር ሲያስፈልገን ያለመጉላላት ሊፈቅድልን ይገባል::

ና ይ ል ፡ - በ መ ጨ ረ ሻ ም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

ዶ/ር መልሰው ንጉሤ፡- ተመራማሪዎች ጊዜና ትኩረት ሰጥተው የምርምር ስራ በመስራት ለሀገራችን እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ መልእክት ማስተላለፍ እፈልጋሁ::

ናይል፡- ስለነበረን ቃለ_ምልልስ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን::

ዶ / ር መ ል ሰ ው ን ጉ ሤ እ ኔ ም አ መ ሰ ግ ና ለ ሁ ፡ ፡



# እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

## THINKING OUT OF THE BOX: TIPS FOR UNIVERSITY LEADERS

*By Asrat Derb*

*PhD candidate in Higher Education Leadership and Management*

*Email: asrat.dereb@bdu.edu.et, or asd.dereb5@gmail.com*


The higher education leadership landscape is now becoming complex and intricate but exhilarating. As a result, the system demands energetic and far-sighted academic leaders. A new generation of higher education leaders may have a more diverse perspective of their institutions' mission and the type of strategies they should identify and execute to be visible nationally and internationally. Leaders should be strategic and thoughtful; at the same time, they should possess the ability to think out of the box if they envision being top in the league table, as most Ethiopian universities declared in their vision statements.

My reflection in this short discourse aims to show some internal and external environmental imperatives that drive universities to go beyond business as usual. Instead, this manuscript invigorates leaders to have top-notch ideas and leapfrog strategies that will transform universities to the highest level. Consequently, holding strategic management concepts and practices help higher education leaders to wisely audit their institutions' internal and external environment and make sound decisions and actions.

In the Ethiopian higher education system, three underlying reasons justify the need for far-sighted leaders that could identify leapfrog strategies and manage them to respond to the national needs and at the same time to be amenable to institutional growth and prosperity. These imperatives are policy enforcement, the universities' motto, and the decline of financial resources. Let's see one by one.

### *1. Policy enforcement*

Regarding policy enforcement, the



HE policy document explicitly states that HEIs should contribute and have huge responsibilities to the country's overall development agenda. Mainly, universities enable the country to be internationally competitive by producing competent graduates who are knowledgeable, skillful, and attitudinally mature. Such a claim is evidenced by the Higher Education Proclamation (FDRE, 2009) objectives. It states:

> Prepare knowledgeable, skilled, and attitudinally mature graduates in numbers with a demand-based proportional balance of fields and disciplines so that the country shall become internationally competitive. (p. 4979).

However, this goal has been slightly adjusted in a recent higher education proclamation 1152/2019.

The three overarching ideas, as mentioned above, articulate the need for quality graduates, the way the graduates are prepared, and the expectations that the graduates contribute to the country. Correspondingly, HEIs should produce competent graduates through demand-based fields and disciplines to remain competitive internationally in economic and social parameters. These are issues that the government entrusted to Ethiopian higher education institutions in shaping their direction accordingly. So, what kind of strategies are needed in the current higher education landscape to discharge such responsibilities?

First and foremost, the higher education system should be tuned to reassure competitiveness.

**The first question here is how Ethiopian higher education institutions view competitiveness?**

Are they really competitive nationally and internationally? In what area should they excel to be competitive? These questions often hit the minds of higher education leaders.

Of course, HEIs view competitiveness through the lens of striving for excellence. In this regard, vision and work ethic are the essential ingredients while an organization strives for excellence. Excellence can be achieved by crafting a good vision for purpose and maintaining employees' strong work habits (Motivated, dedicated, innovative, work in a group) in the organizations (Hill, 2010). Providing freedom for staff to take the initiative and assume responsibility is also one primary element that enables the organization to strive for excellence. Such attributes help staff to demonstrate high-level performance than others. Thus, a competitive university striving for excellence must persistently ignite its quality engine with people, capacity, and resources. Such achievement will be possible if leaders think strategically and create a responsive and robust institution that often audits its environments, designs strategies, and manages them accordingly.

### *2. Universities vision and mission*

The second powerful driving force

**Continued to page 8**

# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

## THINKING OUT OF THE BOX... continued from page 7

that demands strategic thinkers and leaders is universities' visions crafted by themselves. Ethiopian public universities' claims and quest to be ranked in the league table are widely practiced phenomena. This is evidenced in Ethiopian public universities' mission and vision statement that almost all universities promote themselves as competing to be top-ranked universities. Prestigious, excellent, and African Top universities are buzzwords found in many strategic planning documents in Ethiopian Universities. The pursuit of excellence is an essential slogan for organizational success. It motivates and inspires people. Working towards excellence involves a consolidation of quality in everyday activities. The dictionary meaning excellence is 'the quality of being outstanding or extremely good.' Oxford, 2019

When one looks at Ethiopian situations, beginning from first-generation universities to the fourth generation, including the privates' ones, almost all universities in the country, by and large, have a similar vision statement: ranking or striving for excellence. It is not easy to get a specific area where universities excel except a few universities. Seemingly, emerging universities reproduced their visions from the forerunner universities. Replicating might not be a bad practice in academia, but it requires careful examination of the internal and external environment in which the universities operate. It demands the leader's capacity to make situational analysis, i.e., extrapolation of the past, assessing the current practices and determining the future undertakings.

In this regard, it is good to find out universities' strategic management practices that accelerate their ranking ambitions and ensure competitiveness nationally and internationally. Since being top in Ethiopia, Africa or elsewhere necessitates breakthrough strategies and executing capable leaders and incumbents. Besides, such vision statements enforce to explore the measurement strides that universities employ to see their relative positions over time in the

path of vision for success.

Similarly, it would be good to determine the system-wide strategies that track everyday changes within the universities.

Trucking results could be possible if the universities fully adhere to strategic management principles and practices, including having a robust evaluation system. Such practice may help leaders focus on critical strategic issues, systematically track results, and eventually manage discrepancies.

### *3. The decline of financial resources*

The third point that I want to emphasize the need for strategic management in higher education is the decline of financial resources. The availability of sufficient financial resources is one of the necessary instruments for universities to boost their competitiveness. Hence, it is time for Ethiopian universities to think strategically to secure multiple sources of funds for the system's effective functioning.

Let me figure out three justifications for my argument. According to the world bank report, the first scene is that the share of public universities' budget from the national GDP has decreased for the last four to five years. Second, recently, the government enacted a new directive to cut costs across all federal public agencies, including universities (MoFED, 2017). Cutting costs might bring difficulties in Ethiopian higher education institutions since they entirely depend on government funding. Third, introducing a cost-sharing scheme to public universities signals the government's tendency to decline public expenditure on higher education (FDRE, 2003).

Thus, the above three rationales justify the decline of financial resources from time to time. Such inadequacy of funds from the government would create discrepancies to meet the needs and interests of the ever-increasing number of students and staff in the sector. At the same time, it will be a bottleneck in accomplishing their vision and missions.

All the above ventures will force universities to think differently to secure resources to function appropriately and become competitive. Finding alternative means of financing and bringing all resources together to assure the path to excellence and remaining competitive in and gaining competitive advantages is the duty and responsibility of university leaders. Therefore, it is essential to seek alternative financial resources that enable universities to compete nationally and internationally. According to history, around the 1980s, one of the driving causes for the advent of strategic management in higher education was the decline of resources. (Keller, 1983).

Thus, thinking out of the box and becoming strategic is a sine qua non of the current leadership. A new generation of higher education leaders must have leadership competencies to consolidate people, capacity, and resources.

> "A competitive university striving for excellence must persistently ignite its quality engine with people, capacity, and resources."

# ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## የተማሪዎች የፈጠራ ውጤት

በሙሉጌታ ዘለቀ

ከሰብል እና ከዓሳ ቆዳ ተረፈ ምርቶች የፈጠራ ስራዎች የሰሩ የዩኒቨርሲቲያችን ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳድረው ላስመዘገቡት ውጤት የሽልማት እና የእውቅና ፕሮግራም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም ግቢ ጥር 23/2014 ዓ.ም ተካሄዷል።

ሀገር በቀል መፍትሄዎችን ከማምጣት አንፃር የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም የቢዝነስ ኢንኩቤሽን እና ቴክኖሎጅ ኢንተርፕርነርሺፕ ሴንተር (BiTec) ተማሪዎች ከዳጉሳ ገለባ፣ ከገብስ ገለባ እና ከሩዝ ገለባ የወረቀት፣ ከአኩሪ አተር ተረፈ ምርት ኮላ / ማጣበቂያ / እንዲሁም ከዓሳ ቆዳ ተረፈ ምርት የመዋቢያ ሎሽን የፈጠራ ስራ ስራዎች በማቅረብ በሀገር አቀፍ የውድድር መድረክ ላይ ተሳትፈው አሸናፊ ሆነዋል።

ለዚህ ስኬት በገንዘብና በማቴሪያል ድጋፍ ላደረጉ ለGiZ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች የሽልማትና የእውቅና አሰጣጥ ስነ-ስርዓት መካሄዱን የተቋሙ ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ ተናግረዋል።

የቢዝነስ ኢንኩቤሽን እና ቴክኖ ኢንተርፕረነርሺፕ ሴንተር (BiTec) ዳይሬክተር ዶ/ር አማረ ካሳው ተማሪዎች ያላቸውን የፈጠራ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ግምገማ ተደርጎ በስልጠና እንዲዳብር ተደርጎ የናሙና ስራው ከተሰራ በኋላ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ ቢዝነስ የሚቀየሩ የፈጠራ ስራዎችን ውድድር ሲያወጣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አምስት የፈጠራ ስራዎችን አሳትፏል፡

በዚህም መሰረት ሦስቱአሸንፈው ተሸላሚ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ተማሪዎች እናሰራተኞች ቴክኖሎጂዎችን በማሳደግ እና በመፍጠር ወደ ቢዝነስ እንዲሸጋገሩ እና የስራ እድል እንዲፈጥሩ በBiTec ስር የኢኖቬሽን ባህልን ለማሳደግ የሚረዳ BiT Maker Space አቋቁሞ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በእውቅና እና በሽልማት አሰጣጥ ስነ-ስርዓቱ ላይ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር እሰይ ከበደ ተገኝተው ለተሸላሚዎች የእንኳን ደስ ያላችሁ እና የማነቃቃቂያ ንግግር አድርገዋል።



ተማሪዎች ከአሳ ቆዳ ተረፈ ምርትየሰሩት የመዋቢያ ሎሽን በሀላፊዎች ሲጎበኝ




ተማሪዎች የዳጉሳ፣ የሩዝ እና የገብስ ገለባን በመጠቀም የሰሩት ተሸላሚ ያደረጋቸው የወረቀት ስራ በሀላፊዎች

# ጤንነት

## የጉበት ስብ ክምችት በሽታ(Fatty Liver Diseases)

በዶ/ር ኃይለማሪያም የውስጥ ደዌ ህክምና ረዳት ፕሮፌሰር
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ




ትርጉም፡- ከርዕሱ እንደሞንረዳው የሥብ ክምችት በጉበት ውስጥ ከመጠን በላይ ሲሆን የሚከሰት ነው::

ይህም ችግር በጉበት የሚመረተው የሥብ (ቅባት) መጠንና የሚወገደው ቅባት መጠን አለመመጣጠን የሚያመጣው ችግር ነው::

የችግሩ መንስኤዎች ይችላል/የሚከተሉትሊሆኑ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡-

በጉበት ውስጥ ያሉ ህዋሳቶች የስብ አፀግብሮችን በትክክል ማካሄድ ሳይችሉ ሲቀሩ፣ ከመጠን በላይ ስብ ሲመረት ወይም ከመጠን በላይ ስብ ወደ ጉበት ሲገባ፣

የጉበት ህዋሳቶች የተመረተውን ስብ በትክክል ከጉበት እንዲወጣና ወደ ሌላ ህዋሳት ክፍል እንዲሸራሸር ማድረግ ሳይችሉ ሲቀሩ::

የችግሩ መነሻ ምክንያቶች

ከ60 ግራም መጠን በላይ አልኮል በቀን በመጠጣት፣

ሌሎች በሽታዎች እንደ ውፍረት(በተለይ የማዕከላዊ ሰውነት ውፍረት)፣ የስኳር በሽታ፣የምግብ እጥረት እና ሌሎች፤

ልዩ ልዩ መድሃኒቶች፣

በእርግዝናም ሊፈጠር ይችላል፣

ሆኖም ግን የችግሩ መነሻ በአብዛኛው የአልኮል መጠን ነው::

### የበሽታው ምልክቶች

ድካም፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ የሆድ ህመምና የዓይን ቢጫ መሆን፤

የችግሩ መጠን ከፍ እያለ ሲሄድ ደግሞ የሆድ እብጠት እና የእግር እብጠት ያመጣል፤

የጉበት እብጠት ሊከሰት ይችላል፤

ከፍ ሲልም በአፍ ደም መምጣት (የጨጓራ መድማት)፤

ህሌናን መሳት ሊያስከትል ይችላል::

የ ጉ በ ት ም ር መ ራ

ደም ከጉበት ናሙና በመውሰድ እና በልዩ ልዩ ምስል ምርመራዎች ይካሄዳል::

### የህክምናአይነቶች፡-

መጠጥ ማቆም ወይም የችግሩን ምንጭ ማቆም ወይም መቀነስ፣

ክብደት መቀነስ ከ10% ያላነሰ፣

የተመጣጠን እንቅስቃሴ ማድረግ፣

አመጋገብን ማስተካከል፣

ፍቱን የተባለ መድሃኒት ባይኖረውም የስብ መቀነሻ መድሃኒቶችና የተለያዩ ንጥር ነገሮች ሊጠቀሙ ይችላሉ::

### የ በ ሽ ታ ው ደ ረ ጃ ዎ ች

ይሄ በሽታ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት

እነዚህም፡-

የስብ ክምችቶች ብቻ (Simple steatostais)፣

ቁስለት ያለው የስብ ክምችት (Steatohepatitis)፣

ከፍተኛ የሆነ የጉበት ጠባሳ(Cirrhosis)፣

የህመሙ የመጨረሻ ውጤት

የመጀመሪያ ሁለቱ ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ነበረበት ጤናማ ጉበት ሊመለሱ ይችላሉ፤ ስለሆነም ሁሉም መንስኤዎች ቶሎ በማስወገድ እና የላይኞችን ምክሮች መተግበር ያስፈልጋል::

የመጨረሻው ደረጃ ግን ሙሉ በሙሉ ሊመለስ የሚችል አይደለም፤ መሻሻል ግን ይኖረዋል::

አንድ ጊዜ ከጠፋ በኂላ የመመለስ እድል ስለሚኖረው ከላይ የተዘረዘሩትን ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ይኖርብናል::

---

## እንኳን ደስ አለን!!

በጥበበ ግዮን ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከ04/06/2014 ዓ.ም ጀምሮ ኢንዶስኮፒ (የላይኛው አንጀት ክፍል ምርመራ) አገልግሎት መጀመሩን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው::




የጥበበ ግዮን ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የጽኑ ሕክምና አገልግሎት ክፍል ተጨማሪ ዘመናዊ የመተንፈሻ መሳሪያዎችን በማስገባት የላቀ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው ::



# ኪነጥበብ እና ባህል

## ነገረ ሒስ

በበላይ መኰንን (ሊቀ ኅሩያን)

ከሥነ ሒስ ጥበብ ጋር ትውውቅ ሲያንስ ትችታችን ተገቢ ባልኾነ ነቀፋ የታጀበ ኾኖ የመገኘት ዕድሉ ሰፊ ነው:: ትችቱ የደራሲውን ሥራ ወይም የጸሓፊውን ጽሑፍ ሳይኾን፤ ሰብእናውን ወደ መንካት ያዘነብላል። አንዳንድ ሐያስያን የሚተቹትን ሐሳብ፣ መጽሐፍ ወይም ጽሑፍ ሚዛን ላይ አስቀምጠ ጥንካሬና ድክመቱን አያሳዩም ሊያመሰግኑ የፈለጉትን ግለ ሰብእ ወይም ሥራውን ግዝፈት ይሰጡታል:: በአንጻሩ ሊነቅፉት የፈለጉትን ሰው ደግሞ ለስሜት የሚኀረብጡ ቃላትን እየተጠቀሙ ያኮስሱታል። ይህ እንግዲህ ከሒስ ጥበብ ጋር አለመተዋወቅና የንባብ ባህላችን አለማደግ የሚያስከትለው አጉል የሒስ ልማዳችን ነው።

ባለፈው ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም አንድ ወንድሜ በእጅ ስልኬ ላይ ደውሎ ‹‹ልታየው የሚገባ መጽሐፍ ታትሞ ገበያ ላይ ውሏል፤ ብታየው መልካም ነው” ብሎ ጋበዘኝና መጽሐፉ እጄ ውስጥ ገባ።

በመምህር ዳግማዊ ሙሴ የተደረሰው መጽሐፍ ሁለት ርእስ ያለው ሲኾን፤ ዋናው ርእስ ‹‹መጽሐፈ ምንኃር›› ንኡስ ርእሱ ደግሞ ‹‹ኢትዮጵያና ምሥጢረ ግዕዝ›› የሚል ነው:: ‹‹ምንኃር›› የሚለው ቃል ብዙ ያልተለመደ ቢሆንም በዋናነት ቃሉ ‹‹ነኀረ›› አኮረፈ፣ ተቆጣ፣ አንኮራፋ ተብሎ ከሚፈታ ግስ ተወስዶ ‹‹ምንኃር›› መስኖ፣ ወንዝ ወይም ፏፏቴ የሚል ፍች አለው።በደራሲው ብያኔ ደግሞ ‹‹በዕፀ ሕይወት ሥር ያለ ንጹሕ ምንጭ›› የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል።

ይህ መጽሐፍ በጣም የተደከመበት ሥራ መኾኑን ተረድቻለሁ:: ከቀመር አጠቃቀም ጋር ተያይዞም ልረዳውና ልመረምረው የሚገባኝ ብዙ ቁም ነገር አግኝቼበታለሁ:: ከሁሉም በላይ ‹‹ግዕዝ›› የሚለው ቃል በ‹‹አልፋው—አ›› ‹‹ግእዝ›› ተብሎ ነው መጻፍ አለበት የሚሉ ምሁራንን አተያይ በሥነ አመክንዮ ሞግቶ አሳማኝ መልስ ስለ ሰጠ በጣም ተስማምቶኛል።

አሳማኝ ምክንያት ሳይኖራቸው ‹‹ግዕዝ›› የሚለው ቃል ‹‹ግእዝ›› ተብሎ መጻፍ አለበት ብለው የሚሞግቱ ምሁራን አሉ:: እንደ ማሳመኛ ነጥብ የሚጠቀሙት የታላቁን ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን አስተሳሰብ ማለትም ‹‹ግእዝ አንደኛ፣ ቀዳማዊ፣ አዳማዊ ቋንቋ›› ማለት ስለ ኾነ በ‹‹አልፋው -አ›› መጻፍ አለበት የሚለውን በመከተል ነው። ቃሉ በ‹‹አልፋው -አ›› ስለ ተጻፈ አንደኛ፤ በ‹‹ዐይኑ -ዐ›› ስለ ተጻፈ ዐሥራ ስድስተኛ ሊኾን አይችልም:: ምክንያቱም በግዕዙ የፊደል ተራ ፍቺ እንስጠው ከተባለ በማዕከላዊ ድምፁ በ‹‹አሌፉ-አ›› ሳይኾን፤ በመነሻ ድምፁ በ፫ኛው ፊደል፣ በ‹‹ገ›› ነው።

ምክንያቱም ቃሉ ‹‹ገአዘ- ግእዝ›› ይባላል እንጂ ‹‹አገዘ - አግዝ›› አይልምና:: መነሻ ድምፁ ‹‹አ›› ሳይኾን ‹‹ገ›› ነው ለማለት ነው። ወይም ቃሉ በፊደል ተራ ይጻፍ ቢባል እንኳ በ‹‹ገ›› እንጂ በ‹‹አ›› ተራ አይጻፍምና።

ይህ በዚህ እንዳለ፤ ‹‹ግእዝ›› የሚለው ቃል አመል፣ ፀባይ፣ ልማድ፣ ሐሳብ፣ ኹኔታ ወይም ክርክር፣ ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ ውዝግብ ተብሎ ይፈታል። ‹‹ግዕዝ›› የሚለው ቃል ግን ሴማዊ፣ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ ቋንቋ፣ የፊደል መጀመሪያ፣ (ሀ ለ ሐ መ …)፣ የንባብ መጀመሪያ፣ የዜማ ስም ማለት ነው። ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች (ግዕዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ) አንጻር ስንመረምረው፤ በእግዚአብሔር አብ የተመሰለው ‹‹ግዕዝ ዜማ›› አንደኛ፤ በእግዚአብሔር ወልድ የተመሰለው ‹‹ዕዝል ዜማ›› ኹለተኛ፤ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተመሰለው ‹‹አራራይ ዜማ›› ሦስተኛ መኾኑ የታወቀ ነው።በፊደል ገበታችንም አበገደ … ወይም ሀለሐመ … በሚለው የፊደል ተራ የመጀመሪያው ፊደል ‹‹ግዕዝ›› ስለሚባልና ‹‹ሀ - ግዕዝ፣ ለ- ግዕዝ፣ ሐ- ግዕዝ፤ መ- ግዕዝ …›› እያልነ ስለምንማረው፤ ‹‹ግዕዝ›› ማለት ‹‹ቀዳማዊ፣ አንደኛ›› ማለት መኾኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም:: ጀማሪ ጸሓፊ እንኳ ቢጽፈው በየትኛውም የዜማ መጽሐፍ ‹‹ግእዝ ዜማ›› በሚል በ‹‹አሌፉ አ›› ተጽፎ አናገኝም።

የ‹‹መጽሐፈ ምንኃር›› ደራሲ በመቅደሙ ላይ ስለ ‹‹ግዕዝ›› በሰጡት ሐተታ ‹‹ብዙ ጊዜ አብዛኛው ጸሐፍት ግዕዝ የሚለውን ቃል በአልፋው ‹‹አ›› ማለትም ‹‹ግእዝ›› ብለው ነው የሚጽፉት። ያ ግን ፍፁም ስሕተት ነው። ‹‹ግእዝ›› በአልፋው ‹‹አ›› ሲጻፍ ትርጉሙ ነቀፋ፣ ጥል፣ ክርክር ማለት ነው:: ‹‹ግዕዝ›› የሚለው ቃል በዐይኑ ‹‹ዐ›› ሲጻፍ ግን ነጻነት፣ አንድ፣ አንደኛ፣ ሀይማኖት፣ እረፍት፣ ዕለተ ሰንበት እሑድ፣ መጓዝ፣ መጓዣ፣ ወንጌል ማለት ነው›› በማለት ፍቺ ሰጥተውታል። መልካም ነው።ከተዘረዘሩት የፍቺ ቃላት ውስጥ ‹‹ሃይማኖት፣ እረፍት፣ እለተ ሰንበት እሑድ፣ ወንጌል›› የሚሉት በጸሓፊው ስሜት የተሰጡ ይመስላል እንጂ በየትኛውም መዘገበ ቃላት የምናገኛቸው፤ ወይም የመጽሐፍ አስረጅ (ምስክር) ያላቸው አይመስለኝም::

‹‹ግዕዝ›› ከሚለው ቃል አንጻር የመምህር ዳግማዊ ሙሴን ሐሳብ እኔም ስለማምንበት ጥቂት ልበል:: በዘመናችን ከመስማማት መለያየት ይቀናናል፤ ‹‹እኔ ያልኩት ትክክል ነው›› የሚል ስሜት ይገዛናል እንጂ፤ መጻሐፍትንም ሊቃውንትንም ምስክር አድርገን ‹‹ግዕዝ›› በሚለው ቃል መስማማት ነበረብን፡ ፡ ቀደምት አባቶቻችን በሠሩዋቸው ሥራዎች ‹‹ግዕዝ›› የሚለውን ቃል ‹‹በአሌፉ-አ›› ተጽፎ አናገኘውም።

ከታዋቂ ሊቃውንቶቻችንም ከአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በስተቀር ሌሎቹ ‹‹ግዕዝ››ን በ‹‹አሌፍ-አ›› አይጽፉትም። ለግዕዝ ቋንቋ እንደ ጠበቃ የሚቈጠሩት አለቃ አስረስ የኔሰው አንዱ ናቸው:: ከክፍለ ዘመናችን አንጋፋ ምሁራንም አንዱ የሆኑትና ‹‹ነፍሳቸውን ይማርና›› ባለፈው ዓመት የተለዩት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን ልንጠቅሳቸው እንችላለን።

እንደኔ በአካል ባላውቃቸውም በግዕዝ ቋንቋ እና በብራና መጻሕፍት ጥናትና ምርምር ላይ እንደ እርሳቸው የደከመ ሰው አለ ብዬ ስለማላስብ ነው።በ20/21ኛው ምእት ዓመት ከተነሡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (አቡነ መልከጼዴቅ) ‹‹ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህት›› የሚለው መጽሐፍ አዘጋጅ፤ ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሳ ‹‹ያሬድና ዜማው›› የሚለው መጽሐፍ አዘጋጅ፣ መሪ ጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ ‹‹ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ›› የሚለው መጽሐፍ አዘጋጅ እና ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው ተጠቃሽ ናቸው።

እንዲሁም ቀሲስ ዶ/ር አምሳሉ ተፈራ ‹‹ነቅዐ መጻሕፍት›› በሚል ርእስ ከ600 በላይ በግዕዝ የተጻፉ የኢትዮጵያ መጻሕፍትን ያጠኑ ምሁርና ሌሎችምያልጠቀስኳቸው ምሁራን ‹‹ግዕዝ›› የሚለው ቃል በ‹‹ዐይኑ-ዐ›› መጻፍ እንዳለበት ተስማምተውበሥራዎቻቸው አሳይተውናል።

ነገሩ ከተነሣ ዘንድ ነው እንጂ የዚህ ጽሑፍ ዋና መነሻ በምናከብራቸው ሊቃውንት አባቶቻችን ላይ የ‹‹መጽሐፈ ምንኃር›› ጸሓፊ ሥራቸውን ለመገምገም ሳይሆን፤ ግላዊ ሰብእናቸውን የሚነቅፍ ሥራ ጽፈው ለአንባቢ ስላደረሱ አስተማሪ የኾነ ሚዛናዊ ሒስ ለማቅረብ ፈልጌ ነው።

ጸሓፊው ገና ከመቅድሙ ‹‹አንዳንድ አላዋቂ ምሁራን ቋንቋውን ከቤተ ክርስቲያንና ከአምልኮ ጋር ብቻ በማያያዝ …›› የሚል ሐረግ እናገኛለን። (ገጽ 17)

እዚህ ላይ ‹‹አላዋቂ›› የሚለው ቃል አስፈላጊ አልነበረም።

## የደም ውርስ

ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም፣
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም
አጥንት የገካበሽ ደም ያፀናሽ ሀገር፣
የልጆችሽ ህብረት የሆነልሽ ማገር፣
ጎልያድ ነኝ ያለው ፣ ፈታኝሽ ቢበዛም ጠላትሽ ቢቆጠር ዳዊት
ኩተኳሱ-
ፈጣሪውን አምኖ ወንጭፉን ካኳሳ
ሚካኤል የያዘው ይወድቃል በጠጠር።
ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፣
ብዩ ዘምሪያለሁ ብዩ እዘምራለሁ፣
በደም ላከበሯት በአጥንት ለካቧት፣
ክብር እሰጣለሁ ፣ደም ባንዱ ልቤ ፣
ለነገዋ ኢትዮጵያ በደሙ ሚያከብራት ሰው እፈልጋለሁ፣
አለ? ወይስ የለም? እራሴን እጠይቃለሁ ::
አለ ልል እልና፣ የደም ስሩን ባንቧ በጫት በሲጋራ፣የበጠሰ ወጣት
አሻግሬ ኢያለሁ፣ግን እሱም ፣
ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም እያለ ይዘምራል ::
ከአባቱ የዘከነው የጀግንነት መንፈስ ፣
ከልቡ ላይ ወቶ ምላሱ ላይ ንሯል ፣
አባት በትላንቱ ለልጁ ማደሪያ ፣
አጥንቱን ከስክሶ ዛሬን አለስልሶ ለነገው አኑሯል
ልጅ፦
ያባቱ ስጦታ ወርቅ ሆኖ ሳለ ፣
በእጁ ስላገኘው እንደ መዳብ ቆጥሯል ፣
ነገ የራሱ ልጅ እንደምን ይናገር እንዴት ይዘምራል ::
በ ኢያቶቻችን ደም ተከብረሽ የኖርሽ፣
በጫት አዳክሞ ነው ፣
በዘር ከፋፍሎ ነው አባቴ ያስደፈረሽ እያለ ሊዘምር?
የለም የለም የለም !!!
ምንም ሱስ ቢያጠቃው፣
ምንም ቢልፈሰፈስ፣
ስጋውን ከረታው ከዘር ጫት ሲጋራ፣
ልቡን ያሸነፈው ይበልጣል ያገር ሱስ።
እምዩ ስምሽ ሱስ ቢተውት የማይተው፣
እናቴ እቅፍሽ ሱስ ቢለቁት የማይለቅ ፣
ኢትዮጵያየ ሱስ ነሽ ሙዳይ ነሽ የሻሽ ወርቅ።
እናም እናንዮ፦
የበኩር ልጆችሽ ለክብርሽ ለስምሽ ስለተዋደቁ፣
ሳይደርቁ ሳይለዙ በልባችን ሀገር ተተክለው ፀደቁ።
እኛም ፣ተከታይ ልጆችሽ ፣
ለቀጣዩ ትውልድ መንገድ እንጠርጋለን ፣
ታሪክን ከማውሳት አብዜ ተላቀን ታሪክ እንሰራለን ፣
የልጅ ልጆቻችን የሚዘምሩልን ኢያት እንሆናለን ፣
የጅብደኛን መዝሙር ጅብድ በመፈፀም እንቀይራለን።
ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣
ዛሬም ታብቢያለሽ አጥርሽ ነው የኛ ደም፣
ላንች የማንሰጠው የማንሆነው የለም፣
በክንዳችን መሬት ኑሪ ለዘላለም፣
ሊቀጥፍሽ ቢፈልግ ጥንዳ እና ምቀኛ፣
እስትንፋስሽ ሆነን ትኖሪያለሽ በኛ።

ዳግም (ደግ ሰው)ይልማ
ከይባብ ግቢ
2014 ዓ/ም

በቀጣይ እንደ ማሳያው የሚነቀፉት ደግሞ የሀገራችን ምሁራን ናቸው፡ ፡በገጽ 20 ላይም ‹‹በዚህም ምክንያት ፊደላቱ ሞክሼ እየተባሉ በመጠራታቸው በአላዋቂዎች ዘንድ አያስፈልጉም እስከ መባል ተደረሰ›› የሚል ጥቅስ አለ፡፡

እኔ በግሌ ‹‹ፊደላቱ መቀነስ የለባቸውም›› የሚለውን ሐሳብ በየመድረኩ፣ በየዐውደ ጥናቱ ሳቀነቅን እንደ ኖርኩ፤ ‹‹ሕያው ልሳን ግዕዝ- አማርኛ መዝገበ ቃላት›› እና ‹‹ትንሣኤ አማርኛ ግዕዝ መዝገበ ቃላት›› በሚል ርእስ ባሳተምኳቸው መጽሐፍቶቼ በጉልህ እንዳስቀመጥኩ ብዙዎች ይረዱኛል፡፡ ያም ሆኖ ‹‹ፊደላት ይቀነሱ›› ያሉ ምሁራን አላዋቂዎች ኾነው ሳይኾን የራሳቸው ምክንያት ስለሚኖራቸው ነው፡፡

ፊደላትን በመቀነስ ኢትዮጵያን (ትውልዱን) ለመበደል ሌላ ተልእኮ ኖራቸውም አይደለም፡፡ ከተጠቀሱት ምሁራን አንዱ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዐለማየሁ እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ሊከፍሉላት የታገሉላትን፤ በጠላት ተማርከው የታሰሩላትን ኢትዮጵያን ‹‹ፊደል በመቀነስ ሤራ ሠርተውባታል›› ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

በገጽ 43 ላይ ‹‹ምስጢረ ፊደል ያልጠነቀቁ በስም ግን ምሁራን ነን ባዮች ፊደላቱ አንድና ተመሳሳይ እየመሰሏቸው ሞክሼ በማለት ይጠሯቸዋል›› ይላል፡ ይህም ድፍረት ነው፡፡

እውነቱን ለመናገር የታላቁን የታሪክ ተመራማሪ የተከበሩ ተክለ ጻድቅ መኩሪያን ሥራዎች በረቂቅ ቅጂም በመጽሐፍ ጥራዝም ያገኘዋቸውን መጻሕፍቶቻቸውን አንብቤአለሁ፤ ተምሬባቸውማለሁ፡ በመምህርዳግማዊ ሙሴ መጽሐፍ የተጠቀሰውን ‹‹የግብጽ፣ የሳባና የኢትዮጲያ ፊደሎች ማስታወሻ ቁጥር አንድ›› የሚለው መጽሐፋቸው ግን አላጋጠመኝም፡፡ በዚህ መጽሐፍ መነሻነት ታላቁ የታሪክ አባት ተገቢ ላልኾነ ትችት ቀርበዋል፡፡ ከዐለም የሥነ ጽሑፍ ታሪክ አመጣጥ ጋር ተያይዞ ‹‹ዛሬም ያገራችንና የሌላውም ዐለም ያልሰለጠነው አገር ባላገር ብለው የጻፉትን ‹‹ሕዝባቸውን ያልሰለጠነ የሀገራችን ባላገር ባለውታል፤…›› በማለት ባለውለታችን በሕዝብ ለማስጠላት ተሞክሯል፡፡ ይህ ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ የከፋ ገለጻም አለ፡፡ ‹‹የነከኔ በላይ ዐዋቂ ላሳር መዛግብትን አንብበው እንደ ወረደ አምነው በማስቀመጥ ትውልዱን የመመራመር ዕድል እንዳያገኝ ሕይወት የተለየው ሬሳ አድርገው ከፍነው ገንዘው አጋድመውት አልፈዋል›› (ገጽ 87)፡፡

ሥርዓተ ጽሕፈትን ባልጠነቀቀው በዚህ ጽሑፍ የነ ‹‹ከእኔ በላይ ዐዋቂ ላሳር›› የተባሉት ፈረንጆቹ መሰሉኝ፡፡ ‹የነሱን መዛግብት አንብበው እንደ ወረደ አምነው›› የተቀበሉት ደግሞ እነ ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያና አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መኾናቸው ነው፡፡ እነዚህ ታላላቅ አባቶች ለትውልድ ብርሃን ኾኑ እንጂ ሕይወት የተለየው ሬሳ አላደረጉትምና ለዚህ ነቀፋ ንስሓ ያስፈልገዋል፡፡

የጸሓፊው ስሜት ለግዕዝ ቋንቋና ለፊደሉ ከመቆርቆር ባለፈ የእምነት ጉዳይም ያለበት ይመስላል፡፡ በጊዜያቸው ሠርተው ያለፉ አባቶቻችን የሃይማኖት ሕጸጽ ነበረባቸው ቢባል እንኳ ወቀሳውን ለፈጣሪ መተው ነው እንጂ ሙታንን በመጥላትና በመውቀስ የምናተርፈው ነገር የለም፡፡ ሰው ፍጹም ባይኾንም በዘመናቸው ለሀገሪቱ ይበጃል ያሉትን በጎ ነገር ኹሉ ሠርተው ያለፉ ታላላቅ መሪዎችን ታሪክ በማጠልሸት የዘመናችን ሤረኛ ፖለቲከኞች አሰልችተውናልና ከዚህ፣ ሙታንን ከመጥላትና ከመውቀስ በጎ ያልኾነ ልማድ መውጣት አለብን፡፡

> “በተባ ብዕር፣ በነጠረ ዕውቀት ተከራክሮ ማሳመን፤ ሐሳብን በሐሳብ መሞገት ነው እንጂ፤ በአጉል ተቆርቋሪነት መብሰክሰክ አያስፈልግም። በተለይም ትችታችን በትሑት ስብእና፣ በቃለ ትሕትና የተሸመነ መኾን አለበት። ቃለ-ድፍረት መጠቀም በጎ ልማድ አይደለምና። የሒስ ጥበብ ሥነ ምግባርም ይህንን አይፈቅድም።’’
>
> በላይ መኰንን (ሊቀ ኅሩያን)
> ደራሲ እና የአማራ ደራሲያን ማህበር ፕሬዜዳንት

ጸሓፊው እንደሚያስቡት የተጠቀሱት ምሁራን የጻፉት ሥራቸው ለትውልድ ማሰናከያ ይኾናል ብለን የምናስብ ከኾነ በሚዛናዊ ሒስ ሥራቸውን እየ ተቸን ትውልድ እንዲማርበት እናድርግ፡፡ አለበለዚያ ‹‹ቅኔው ቢጠፋበት ቀረርቶ ሞላበት›› እንደሚባለው የማይገባ ቃለ ጽርፈት አንጠቀም፡፡ ሆህያትን፣ ቃላትን፣ ሥርዓተ ነጥቦችን ወዘተ ጠንቅቀን ሳንረዳ ጥንቁቆችን ሊቃውንት በስሜት ለመተቸት አንቸኩል፡፡ እንደኔ ችግራችን እነሱ ሳይኾኑ እነሱን የሚተካ ጥንቁቅና ትጉህ ትውልድ ማጣታችን ነው፡፡

ለስሜቴ ከከበዱኝ ጥቂቶችን እያረምኩ ላቅርባቸው፡፡‹‹ታላቁ ጸሐፊ [ጸሓፊ] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ [መኵሪያ] እንዲህ ያለ ምስጢር የያዘ ፊደላቸውን ሳይረዱ እነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በቀደዱላቸው የተንኮል ቦይ ተከትለው እየፈሰሱ ኖረዋል፡፡ ይህም የጥፋት መስመር አገራቸውን ረስተው የስልጣኔና የሥነ-ጽሑፍ [የሥነ ጽሑፍ] ፍልስፍናን ለፈርያኖቹ ሰጥተው እስኪጽፉ አድርሷቸዋል›› (ገጽ 91)፡፡

‹‹አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከራሳቸው አልፎ አገራቸውን፣ ፊደላቸውን፣ አንባቢያቸውንና ተተኪ ትውልድን ለቅኝ ግዛት አሳልፈው ከሰጡ በኋላ …›› (ገጽ 100)

‹‹የቅርብ ሩቅ የኾነ ባለጋራም ከውስጥ ኾኖ ወገን መስሎ ብዙ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ለዚህም ኹነኛ ተጠቃሽ አለቃ ኪዳነ ወልድ ናቸው፡፡ ግዕዝን በመናገርና መጻፍ የቤተ ክርስቲያን ሰው በመምሰል አንዲት፣ ርትዕትና ቅድስት በሆነች ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ሀይማኖት ላይ ድብቅ ምንፍቅናቸውን ለመጫን ያልቆፈሩት የክፋት ጉድጓድ፣ ያልፈነቀሉት የተንኮል ድንጋይ የለም›› (ገጽ 151)፡፡

ከዚህ በላይ ለተባሉት ነገሮች ኹሉ ሌላ ነገር ሳልል፤ ጸሓፊውን፣ አርታዕያንና አንባብያንንም ጭምር አምላከ አበው ይቅር ይበለን!!

በዚህ መጽሐፍ (መጽሐፈ ምንኃር) በምስጋናዐምድላይስማቸውየተጠቀሰ የምናውቃቸው የቤተ ክርስቲያንችን ምሁራንን ስም አይቻለሁ፡፡ ተጠራጠርኩ፤ ወይ ዐላዩትም፤ ወይ ዐይተው አላዩትም የሚል ስሜት መጣብኝ፡፡ ምክንያት አለኝ፡፡

በአለፉት ስድስትና ሰባት ዓመታት በዐማራ ደራስያን ማኅበር ስሠራ አንዳንድ ጀማሪ ገጣምያን ወይም ደራስያን እንድመክራቸው ይጠይቁኛል፡፡ እኔም ከጊዜ ዕጥረት አንጻር ሥራቸውን በዝርዝር ሳላየው አጠቃላይ የኾነ ሐሳብና የሥነ ጽሑፍ አላባውያንን በመንገር አማክራቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ ታትሞ ሲወጣ ስሜን በምስጋና ዐምድ ላይ በጉልህ ተጽፎ አገኘውና፤ ወደ መጽሐፉ የመጀመሪያዎቹ ገጾች ገለጥ፤ ገለጥ አድርጌ ስመለከት የፊደል፣ የቃላት፣ የሥርዓተ ነጥብ ወዘተ. ግድፈቶችን ሳገኝ እደነግጣለሁ፡፡ ስሕተቱን እኔ እንደሠራሁትም ይሰማኛል፡፡ ምን ለማለት ፈልጌ ነው? አንዳንዱ የታወቁ ጸሐፍት ወይም ደራስያን ስም በምስጋና ዐምድ ላይ መጥቀስ መጽሐፉ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረጊያ ስልት እየ ኾነ ስለ መጣ ብዙ ባላዩት ሥራ ላይ ስማቸው ሊጠቀስ ይችላል ለማለት ነው፡፡

ጸሓፊው ገና ከመግቢያው ላይ ሲገልጹ ‹‹ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያነሣሣኝ ዋና ምክንያት ብስጭት፣ ንዴት፣ ቁጭትና እልህ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ የኾነ ኹሉ የእኔን ሕመም እንዲታመምልኝ ባልጠይቅም ሕመሜ እንዲሰማው ግን እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም የሕመም ሕመም፣ የሞት ሞት፣ የሸፍጥ ሸፈጥ፣ የሤራ ሤራ፣ የግፍ ግፍ፣ የበደል በደል፣ በግዕዝ ማንነቱ ላይ የተፈጸመበት የታሪክ ደባ ነው›› (ገጽ 9)፡፡

የተጠቀሱት አባቶች በግዕዝ ላይ ሤራ ሠርተውበታል ብዬ ለመቀበል እቸገራለሁ፡፡ ተሠራበት ቢባልስ የአስተሳሰብ ልዩነት ስለ ኾነ ብስጭት፣ ንዴት፣ ቁጭትና እልህ ምን አመጣው? የሰዎች አስተሳሰብ የኔን ካልመሰለ ብሎ ብስጭት አለ? እንኳን ሥነ ልሳናዊ አስተሳሰባቸው (ዕውቀታቸው) እምነታቸው የኛን ባይመስል የምን ንዴት ቁጭትና እልሕ ነው፡፡ በተባ ብዕር፣ በነጠረ ዕውቀት ተከራክሮ ማሳመን፤ ሐሳብን በሐሳብ መሞገት ነው እንጂ፤ በአጉል ተቆርቋሪነት መብሰክሰክ አያስፈልግም፡፡ በተለይም ትችታችን በትሑት ሰብእና፣ በቃለ ትሕትና የተሸመነ መኾን አለበት፡፡ ቃለ ጽርፈት መጠቀም በጎ ልማድ አይደለምና፡፡ የሒስ ጥበብ ሥነ ምግባርም ይህንን አይፈቅድም፡፡

በሌላም በኩል ‹‹ግዕዝ የቆየ፣ የኖረ፣ ከዓለም ሁሉ ቋንቋ ቀድሞ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ መግባቢያ እንዲሆን የተሰጠ ዓለም የተፈጠረበት ቋንቋ ነው፡፡ …የዕለት ተዕለት ተግባርን መተግበሪያ ብሔራዊ ቋንቋ ነው፡፡ ከነበረው የሥልጣኔ ማማ አውርደው ያጣ የነጣ ዕጓለ መውታ ሆኖ በገዛ አገሩ፤ በገዛ መንደሩ ቀባሪ ያጣ ሬሳ ሆኖ እንዲኖር ያደረጉት የውስጥ ቁንቁኖች በዚህ መጽሐፍ ሚዛንነት ይመዘናሉ›› ይላል (11)፡፡

‹‹ዕጓለ ማውታ ሆኖ በገዛ አገሩ፤ በገዛ መንደሩ ቀባሪ ያጣ ሬሳ ሆኖ እንዲኖር ያደረጉት የውስጥ ቁንቁኖች›› የሚለው በስሜት የገባ አገላለጽ ነው፡፡ በመሠረቱ ግዕዝ ቀባሪ እንዲኖረው ወይም እንዲቀበር ማንም አይፈልግም፡፡ ሬሳም አይደለም ሕያው ነው፡፡

‹‹የውስጥ ቁንቁኖች በዚህ መጽሐፍ ሚዛንነት ይመዘናሉ›› ሲል ‹‹ቁንቁኖች›› [ቍንቍኖች] የሚለው ቃል ባይመቸኝም፤ ከጸሓፊው ሚዛናዊ ሒስ ጠብቄ ነበር፡፡ ነገር ግን ‹‹የውስጥ ቁንቁኖች›› የተባሉት የተጠቀሱት ምሁራን ይኹኑ ወይም ሌሎች በሒስ ሚዛን አልተመዘኑም፡፡

ለነገሩ መመዘን ያለበት ጽሑፋዊ ሥራቸው ኾኖ፤ ነጥብ በነጥብ እየ ጠቀሰ በሥነ አመክንዮ በመተንተን እና ማጠየቂያ በማቅረብ ነው እንጂ ግለ ሰብእናቸውን በመንቀፍ አይደለም፡፡ ይህ በመኾኑም ብዕሬን አንሥቼ መመማሪያ ይኾን ዘንድ ይህን ንፍቀ ጽሑፍ (አረቲክል) ለሐያስያን አቅርቤዋለሁ፡፡

በመጨረሻም፤ ‹‹መጽሐፈ ምንኃር›› የሚለው ሥራ በጣም የተደከመበት፤ ለጥናትና ምርምር፣ ቋንቋውንና ሥነ ቀመሩን ለማጥናት የሚያነሣሣ ሥራ ስለ ኾነ ደራሲውን እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

ይቆየን!!

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርቡበታል

## Bahir Dar Institute of Technology- Bahir Dar University hosted a seminar by an alumni and a System and Robotics Engineer at NASA.




Dr. –Ing Melak Mekonen, a system and Robotics Engineer at NASA Gorrard Flight Center, delivering seminar

Dr. –Ing Melak Mekonen, a system and Robotics Engineer at NASA Gorrard Flight Center, delivered an enchanting seminar. DART (Double Asteroid Reduction Test), Military and Space Robotics, and System Engineering were the topics of his lecture. According to Dr.-Ing Melak's presentation, the major goal of DART was to look at the ways to avoid an asteroid collision on Earth. It was based on the momentum concept, with scientists attempted to change the orbital period and location. NASA examined asteroids, spacecraft, and relative dynamics when testing to capture a 7.3 second variation in the period. However, his presentation focused on asteroids of bigger dimensions, whereas smaller asteroids of up to 4 meters have no significant impact on Earth. The only way to change the orbital period and position was to use spacecraft that collided with the asteroid's center of mass. As a result, the likelihood of achieving higher accuracy rises. Since question regarding to accuracy had been pointed out, he responded with the concept of specified accuracy, which will later be verified and validated. He also noted the DART mission Rocket launched on November 24, 2021 as of today.

Robots, on the other hand, can be either earth-based multipurpose robots or space robots that will be used to recharge and/or replace satellite batteries. Dr. –Ing Melak stated that military robots will be used to investigate future battlegrounds and gather information about the structure, location, and capabilities of the enemy force. Aside to explaining the intension of NASA's mission, Dr.-Ing Melak advocated for teamwork and for senior officials to widen the scope of the vision, but he insisted on work that stands alone as being of high quality.

Finally Dr Seifu Admasu, Scientific Director of BiT, closed the event with kind gratitude notifying the implication of the event by alumni, which is related to the 60th anniversary of Bahir Dar University. At the end Dr. –Ing Melak received a gift on the behalf of BiT.

*NOTICE*
*For post graduate students of BiT-BDU:*

*We are thrilled to announce that three high performance computers (HPC) are installed inside JAN_MOSCOV Library of BiT. The computers are already set up to be accessed from remote location. You can find details from JAN-MOSCOV library.*



# ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ጃን ሞስኮብ ቤተ-መጽሃፍት

በሽጋው መስፍን

ማንበብ ሙሉ ሰዉ ያደርጋል የሚል አንድ የቆዬ አባባል አለ። በርግጥም ማንበብ ሙሉ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ሀገርና ሙሉ ተስፋ እንዲኖረን በማድረግ የተሻለ ትዉልድ እንዲፈጠር ያደርጋል። ነገር ግን አፍሪካውያን የማንበብ ባህላችን "አፍሪካዊያን እንዳያዉቁት የምትፈልገዉን ሚስጥር መጽሐፍ ዉስጥ ደብቀዉ" ተብሎ እስከሚሳለቅብን ድረስ ያልዳበረ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ አይደለም። ይሄ ብቻ አይደለም አፍሪካዊ ምሁራን ዲግሪያቸውን ካገኙ በኋላ ስለማያነቡ ተመልሰው ወደ መሃይምነት ይቀየራሉ በሚል ገፋ ያለ ትችት ውስጥ ወድቀናል።

እውነት ነው ተማሪዎች ፈተና እንደጨረሱ ለፈተና የተዘጋጁበትን ሞጁል ሲያቃጥሉ፣ ሲቀዱ ይስተዋላል። ነገር ግን ዲግሪ ለተወሰነ የትምህርት ስልጠና ዘርፍ የሚሰጥ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም ሰው በማንበብ የማያቋርጠውን እውቀት በየጊዝው ማደስ ይገባዋል።

ውድ የናይል አንባብያን በማንበብ ዙሪያ የተሸከረከርነው የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በየጊዜው በባሕር ዳር ከተማ ከፈጠራቸው ጸጋዎች መካከል ለንባብ ዋና ግብዓት ውስጥ አንዱ የሆነውን ልናስተዋውቃችሁ በመውደዳችን ነው። ለዛሬው ስለ ጃን ሞስኪብ ቤተ-መጽሃፍት ልንነግራችሁ ፈቅደናል።

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የንባብ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ለመስጠት በዉቧ ከተማ ባሕር ዳር እምብርት ላይ ባለ ግርማ ሞገስ ህንፃ ከተንጣለለ ግቢ ጋር አስደናቂ ቤተ-መፃህፍት በመገንባት ለዩኒቨርሲቲዉና ለአካባቢዉ ማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።



ጃን ሞስኪብ ቤተ-መጽሃፍት

በፈረንጆች አቆጣጠር በ1959 የኢትዮጵያ የቀድሞ መሪ የነበሩት ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ (ቀ.ኃ.ሥ.) (ጃንሆይ) በሩሲያ ዋና ከተማ ሞስኮ ጉብኝት አካሂደዉ ነበር። ከሞስኮ አቻቸዉ ከኒኪታ ክሩሽቸቬ ጋር ባደረጉት ዉይይት ሶቪየት ህብረት ኢትዮጵያን በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ለማገዝ የሚቻልበት ስምምነት ተደርሶ ነበር። በዚህም መሰረት ሶቪየት ህብረት አንድ የቴክኖሎጂ ትምህርት ቤት ለኢትዮጵያ ለመገንባት ወሰነች።

ይህም የቴክኖሎጂ ትምህርት ቤት በፈረንጆች አቆጣጠር ታህሳስ 30/1961 በባሕር ዳር እንዲገነባ የመሰረት ድንጋይ በንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ተጣለ።

ትምህርት ቤቱም በ18 ወራት ተገንብቶ በፈረንጆች አቆጣጠር ሰኔ 11/1963 አጼ ኃይለስላሴ በተገኙበት የፖሊቴክኒክ ትምህርት ቤቱ ተመርቆ ስራ ጀመረ። በሶቪየት ህብረት እርዳታ የተሰራ በመሆኑ የአካባቢዉ ነዋሪዎች ትምህርት ቤቱን የሞስኮቭ ትምህርት ቤት እያሉ ይጠሩት ነበር።

ትምህርት ቤቱ በ1992 ዓ.ም ከፔዳጎጂ ኮሌጅ ጋር በመሆን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ፈጠሩ፡ በዚህም የድሮዉ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ቤት የቴክኖሎጂ ተቋም የሚል መጠሪያን አገኘ። የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ተቋም ቤተ-መፃህፍትም አመሰራረት ከፖሊቴክኒክ ትምህርት ቤቱ ጋር የተያያዘ ነዉ።

በአሁኑ ሰዓት ተቋሙ ፣ ግዙፍ እና ዘመናዊ ቤተ-መፃህፍት አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን የዚህ ግዙፍ ቤተ-መፃህፍት ስያሜም ሁለት ስሞችን በማዋሀድ የተፈጠረ ነዉ። እነዚህም ተቋሙ እንዲሰራ ያደረጉትን የወቅቱ የሀገሪቱ መሪ ስም አጼ ኃይለስላሴ (ጃንሆይ) እና ተቋሙ በአካባቢዉ ማህበረሰብ ይጠራበት የነበረዉን የድሮ ስም ሞስኮቭ ትምህርት ቤት በማዋሀድ ለማስታወሻነት ይሆን ዘንድ "ጃን ሞስኮቭ" ላይበራሪ በማለት መጠሪያ ስሙ እንዲሆን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተወስኗል፡

ጃን ሞስኮቭ ቤተ-መፃህፍት በአሁኑ ሰዓት የተቋሙ የዲጂታል ቤተ መፃህፍትን ጨምሮ የተሟላ የ24 ሰዓት አገልግሎት ለተጠቃሚዎች እየሰጠ ሲሆን ግዙፍ እና በጠቅላላው ለዩኒቨርሲቲዉም ሆነ በተናጠል ለባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ተቋም ኩራት የሆነ ባለ አራት ወለል ህንፃ በዉስጡ እያንዳንዳቸዉ እስከ 500 ሰዎችን የሚይዙ 3 ታላላቅ አዳራሾች፣ እስከ 50 ማስተናገድ የሚችሉ 5 ያህል ትንንሽ አዳራሾች ሲኖሩት

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

# ከጅኦስፔስ ሳይንስ ተመራማሪው ጋር የተደረገ ቆይታ

በአለባቸው አለሙ



መልሰው ንጉሴ(PhD)
ዋሽራ ጂኦስፔስ ጥናትና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር

ናይል፡- በመጀመሪያ ለናይል ጋዜጣ የዚህ ወር እትማችን እንግዳ ለመሆን ያቀርብንልዎትን ጥያቄ ተቀብለው ለቃለመጠይቅ ስለተባበሩን በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን:: እስቲ እራስዎትን ለአንባቢያን ያስተዋውቁልን?

እንግዳችን፡- እኔም አመሰግናለሁ:: መልሰው ንጉሴ እባላለሁ:: የተወለድኩት ምዕራብ ጎጃም ዞን በቡሬና በሽንዲ መካከል የሚገኝ ልዩ ስሙም ሰባዳር ሚካኤል የሚባል አንድ የገጠር መንደር ነው:: እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ሰባዳር ሚካኤል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማርሁ:: በመቀጠልም የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል ትምህርቴን ሽንዲ ገብቼ ተማርሁና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርቴን ወደ ቡሬ በመሄድ ከአጎቴ ቤት ሆኜ ቡሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማርሁ::

ከዚያም ጥሩ ውጤት አምጥቼ ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብቼ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በ1996 ዓ/ም ተመርቄ 2 አመት ሰራሁና ተመልሼ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብቼ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን ተማርሁና ከሁለት አመት በኋላ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርቴን በዚሁ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና ጣሊያን ሀገር የሚገኝ የምርምር ኢንስቲትዩት /International Center for Theoretical Physics,ICTP/ የሚባል እየተመላለስሁ የ3ኛ ዲግሪ ትምህርቴን ስፔስ ሳይንስ ተምሬ ጨረስሁ:: በመቀጠል በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፊዚክስ ዲፓርትመንት የማስተማርና የምርምር ስራዬን መስራት ቀጠልሁ::

ናይል፡- በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከማስተማር ስራዎ በተጨማሪ ኃላፊነት አለዎት?

ዶ/ር መልሰው፡- አዎ ዋሸራ ጂኦስፔስ ጥናትና ምርምር ማዕከል ከተቋቋመ ጀምሮ የምርምር ማዕከሉ ዳይሬክተር ሆኜ ነው እያገለገልሁ ነው:: ሌላው በማዕከሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማጠናከር ተማሪዎችን የማስተማር ስራም እየሰራሁ እገኛለሁ::

ናይል፡- የዋሸራ ጂኦስፔስ ጥናትና ምርምር ተቋም ዓላማው ምንድን ነው?

ዶ/ር መልሰው፡- የዋሸራ ጂኦስፔስና ራዳር ሳይንስ ላብራቶሪ የሚባል በፊዚክስ ዲፓርትመንት ከሳይንስ ኮሌጅ ጋር የስፔስ ሳይንስ ጥናቶችን እያደረገ ይገኛል::በመሰረቱ የዋሸራ ጂኦስፔስ ማዕከል የስፔስ ሳይንስ ተግባራዊ የሆነውን ትምህርት በመስጠት ግንባር ቀደም ነው:: ከ2007 እ.ኤ.አ ጀምሮ በዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ነው የተጀመረው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት እያስተማረ ነው የቀጠለው::

በ2017 እ.ኤ.አ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ወደ ጥናትና ምርምር ማዕከልነት አድጎ ጸደቀ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የምርምር ስራዎችን እያደረገ ይገኛል:: በዚህ የጥናት ማዕከል ውስጥ አራት የትምህርት ክፍሎች አሉ::

ስፔስና የአትሞስፌሪክ ፊዚክስ የሚያጠና፤የራዳር ሳይንስን የሚያጠና፤ አስትሮኖሚና አስትሮ ፊዚክስን የሚያጠና ኢንስትሩመንቴሽንና አውቶሜሽን ዙሪያ ላይ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ የትምህርት ክፍሎች ከፍቶ የምርምርና የማስተማር ስራን ማእከል በማድረግ እየሰራ ይገኛል::

ማዕከሉ በዋናነት ከመሬት ጀምሮ ወደላይ ያለውን የአየር ክልል እስከ ጸሐይ ድረስ ጥናት ያደርጋል:: በአጠቃላይ በመሬት አየር ክልል ውስጥ ያሉ ቅንጣት አካላት ማለትም፤ ኤሌክትሮንስና ፖዘቲቭ አይወን የምንላቸውን በጊዜና በቦታ ይቀያየራሉ:: የእነዚህ ቅንጣት አካላት መቀያየር ደግሞ እኛ መሬት ላይ ሆነን የምንጠቀመውን ቴክኖሎጂ ያደናቅፋሉ:: ስለሆነም ስለአደናቃፊ ነገሮች ምንነት ጥልቅ ጥናት ያደርጋል ማለት ነው:: ጠቀሜታውም የሚያደናቅፉ አካላትን በመለየት ከተግዳሮት ነጻ የሆነ ስራ መስራት የሚያስችል ጥናት ነው የሚያደርገው:: ጥናትና ምርምር የሚከናወነዉ ላብራቶሪ ላይ የተገጠሙ መሳሪያዎችን እና ሞዴል በመጠቀም ነው:: ሌላው በአሜሪካውያንና በአውሮፓውያን የመጠቁ መሬትን የሚያሽከረከሩ ብዙ ሳተላይቶችን መረጃም እንጠቀማለን::


ናይል፡- እርስዎ ከሰሞኑ አንድ ከዚሁ ስራዎት ጋር ግንኙነት ያለው የጥናት ፕሮጀክት ማሸነፍዎን ወሬው ደርሶናል፤ እስኪ ስለፕሮጀክቱ ይግለፁልን?

ዶ/ር መልሰው፡- የዚህ ጥናት ፕሮፖዛል የተጻፈው ከመሬት በላይ ከ50 ኪ/ሜ ጀምሮ እስከ 2000ኪ/ሜ ድረስ ወደ ሰማይ በዚህ የአየር ክልል ውስጥ በተፈጥሮ ያሉ ቅንጣት አካላትን ማለትም ኤሌክትሮንና ፖዘቲቭ አይወን የምንላቸውን ቅንጣት አካላት በጊዜና በቦታ ያላቸውን መለዋወጥ መንስኤ ለመፈለግ ነዉ:: ለምሳሌ ባሕር ዳር ላይና አስመራ ላይ ያለውን የቅንጣት ብዛት ብናወዳድረው አንድ አይነት አይደለም፤ይለያያል::በጊዜም በብዛታቸዉም ይለያያል:: ይህ መለያየት ደግሞ ቴክኖሎጂዎችን በትክክል ለመጠቀም አያስችልም::


ለምሳሌ የራዲዮ ኮሚኒኬሽን ስናደርግ እነዚህ ቅንጣት አካላት የምናደርገውን ግንኙነት ያደናቅፉታል::በተጨማሪም ጂ.ፒ.ኤስን ስንጠቀም የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ ለማመልከት ሎንግቲዩድ፤ አልቲቲዩድና ላቲቲዩድ ቅንጣት አካላቱ ችግር ይፈጥራሉ:: ይህም ማለት ጂፒኤስ መሳሪያ በትክክል ልትነግረን ትችል የነበረው እነዚያ ቅንጣት አካላት ባይኖሩ ነበር::

ቅንጣት አካላት በመኖራቸዉ ምክንያት ጂፒኤስ መሳሪያ ስህተት ጨምራ ነው የምትነግረን:: የዚህን መሣሪያ ትክክለኛ ጥቅም ለማግኘት የቅንጣት አካላቶችን ብዛት በጊዜና በቦታ መተንበይ መቻል አለብን:: ይህን ብዛታቸውን እንዲቀያየር የሚያደርገው አንዱ ነፋስ ሊሆን ይችላል:: እነዚያን ቅንጣት አካላቱን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ሲያንቀሳቅሳቸው

ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ከፀሐይ የሚለቀቁ ነገሮች (ቅንጣት አካላት እና ማግኔቲክ ፊልድ) እና የመሬት ማግኔቲክ ፊልድ ግንኙነት::




የመሬት የላይኛዉ አየር ክልል ዉስጥ የሚገኙ ቅንጣት አካላት መለዋወጥ ጅፒስን (GPS) በምንጠቀምበት ጌዜ የሚያስከትሉት ተፅኖ (ደማቅ ቀይ ነው ይህ ከፍተኛ ተጽኖ መኖሩን ያመለክታል)::




የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የካቲት 19 2014 ዓ.ም 383 በቅድመ-ምረቃ፣ 24 በማስተርስ እንዲሁም በሕክምና ስፔሻሊቲ 50 በድምሩ 457 ተማሪዎችን አስመርቋል። ከእለቱ ተመራቂዎች መካከል 187ቱ ሴቶች ናቸው።





